# ከስደት ተመላሾችን ለማቋቋም…!

**ተስፋዬ ለማ** 12/31/13

ስደትን ከስር መሰረቱ ለመፍታት ድህነትን መዋጋት ዓይነተኛ መፍትሄ ነው። ወጣቱ ትውልድ ክብሩና ሰብዓዊነቱ ሳይነካ በሀገሩ የሚፈልገውን ሰርቶ የሚኖርበት ምቹ ሁኔታ ድህነትን ድል ማድረግና የስደትን መሰረታዊ ምክንያት መቅረፍ ልዩ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው። ወጣቱ ትውልድ ስደትን ከመፈለግ ወጥቶ በሀገሬ ሰርቼቸ አገኛለሁ እከብራለሁ የሚል እምነት ማሳደር ይኖርበታል።

ለዚህ ደግሞ መንግስት የስራ እድል ከመፍጠር ጎን ለጎን የአመለካከት ለውጥ ማምጣትና ንቅናቄ መፍጠር እንደሚኖርበት በመረዳት በአገር ደረጃ ብሄራዊ ምክር ቤት በመመስረት መስራት ከጀመረ ሁለት ዓመታትን አስቆጥሯል።

ከአገራችን ወደ ተለያዩ አገራት እየፈለሰ ያለው ወጣት ቁጥርና በሚሄዱበት አገራት እየደረሰበት ያለውን እንግልትና የሰብአዊ መብት ጥሰት ለማቆም በማሰብ በ2004 ዓ.ም በብሄራዊ ደረጃ ምክር ቤት ተቋቁሞ ስራዎችን በእቅድ እንዲመራና በአገራችን ከጉዳዩ ጋር ተያይዞ ያለውን የአሰራር ክፍተት ፈትሾ የተሻለ አሰራር እንዲያሰፍን ያስችላል በሚል እሳቤ ነበር።

በዚህ መሰረትም በ2005 ዓ.ም በርካታ እንቅስቃሴዎች ማድረጉ ይታወቃል። ይሁንና የረጅም ጊዜ እቅድ ነድፎ እየተንቀሳቀሰ ባለበት በአሁኑ ወቅት በሳውዲ ዐረቢያ የመኖሪያ ፈቃድ ሳይኖራቸው የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ከሀገሪቱ እንዲወጡ የአገሪቱ መንግስት በማወጁ የተነሳ እነዚህን ዜጎች ወደ አገራቸው የመመለስና የማቋቋም ስራን እየተገበረ ይገኛል።

በሳውዲ ዐረቢያ ሕጋዊ የመኖሪያ ፈቃድ ማግኘት አይችሉም ተብለው የሚገመቱት ኢትዮጵያውያን ቁጥር ከፍተኛ ነው፡፡

እነዚህ ዜጎች ወደ አገራቸው የማስመለስና የማቋቋም ስራው እጅግ ባጠረ ጊዜ ለማከናወን ሌት ተቀን እየሰራ ይገኛል።

ወደ አገራቸው መመለስ ያለባቸውን ዜጎች በአጭር ጊዜ ውስጥ በማምጣትና ወደየመጡበት አካባቢ በመመለስ የማቋቋምና በተለያዩ የስራ ዘርፎች የማሰማራት ተግባር እንደሚከናወን ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የወጡ መረጃዎች ያሳያሉ።

ሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውር ለዜጎችም ሆነ ለአገሪቱ የማይጠቅም በመሆኑ በአገር ደረጃ መንግስት ህገወጥ የሰዎች ዝውውርን ለመከላከል ብሔራዊ ኮሚቴ አቋቁሞ እየሰራ እንደሆነ ይታወቃል። ኮሚቴው ከሳውዲ አረቢያ ተመላሽ ስደተኞችን በማስመለስና በማቋቋም መደረግ የሚገባው አጠቃላይ አቅጣጫም ከክልሎች ጋር በተደረገ ውይይት በማስረጽ ስራዎች በተቀላጠፈ መልክ እንዲከናወኑ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል።

ችግሩ ከመከሰቱ አስቀድሞም ሆነ ችግሩን ከተከሰተ በኋላ ቀላል የማይባል የሰው ሃይል አሰማርቶ ስራውን በተገቢው መንገድ እያከናወነ ይገኛል። በተለይም እድሜያቸው ለአቅማ ሄዋን ያልደረሱ ሴቶችና ህጻናት በመኖራቸው እነዚህን ዜጎች በአፋጣኝ ወደ አገር ቤት የመመለሱ ስራ ቅድሚያ ተሰጥቶ እየተሰራ ነው።

መንግስትም ጉዳዩን በተፋጠነ መንገድ ለማጠናቀቅና ዜጎችን ለመታደግ 50 ሚሊዮን ብር በመመደብ ሥራውን እያከናወነ ነው፡፡ አለም አቀፉ የስደተኞች መርጃ ድርጅትም ድጋፍ አድርጓል፡፡ እስካሁን 140 ሺሕ የሚደርሱ ስደተኞች ለአገራቸው መሬት በቅተዋል።

በቀጣይም ዜጎቹን በቋሚነት ለማደራጀት በሚሰራው ሥራ ብሔራዊ ኮሚቴ ከክልል እስከ ከተማ የሚሰራውን ስራ በመንደፍና ከክልሎች ጋር ተከታታይ ውይይቶችን በማድረግ የተቀላጠፈ የማቋቋም ስራ በመሰራት ላይ ይገኛል።

ሁሉም ክልሎች ተመላሽ ስደተኞችን የማቋቋሙን ተግባር በማፋጠን ላይ ይገኛሉ። ለአብነት ያህልም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርን በአብነት መውሰድ ይቻላል። ከሳዑዲ አረቢያ ወደ አገራቸው የተመለሱ ዜጐችን በተለያዩ የስራ መስኮች ለማሰማራት በዝግጅት ላይ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል።

የአስተዳደሩ የቢሮ ኃላፊዎች ህገ ወጥ የሰዎች ዝውውርን ለመግታትና ከስደት ተመላሾችን ለማቋቋም መንግስት እያደረገ ያለውን እንቅስቃሴ በማስመልከት ሰሞኑን ባደረገው ውይይት ተመላሾች በየክፍለ ከተማቸው ቅድሚያ ተሰጥቷቸው እንዲቋቋሙ የማድረጉ ተግባር በቅርቡ እንደሚጀምር አስታውቋል።

ከስደት የተመለሱ ዜጎችን በመከታተል አስፈላጊውን ድጋፍ የሚያደርጉ ከሚመለከታቸው አካላት የተውጣጡ ኮሚቴዎች ተቋቁመው ተግባራዊ እንቅስቃሴ መጀመራቸውን ነው፡፡ በዚህም አስተዳደሩ ከሳዑዲ አረቢያ የተመለሱ ዜጎች በቋሚነትና በዘላቂነት በመረጡት የሥራ መስክ በማቋቋም የሥራ ዕድል ለመፍጠር ዝግጅት ማጠናቀቁንም ተገልጿል፡፡

እስካሁን ወደ አገራቸው ከተመለሱ ስደተኞች መካከል አምስት ሺህ የሚደርሱት የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ናቸው፡፡ እነዚህን ተመላሾችን በቋሚነትና በዘላቂነት በማቋቋም የማደራጀትና ሥራ የሚያገኙበት ሁኔታ ቅድሚያ ተሰጥቶት እየተሰራ ነው፡፡

ከስደት ተመላሾች በማኑፋክቸሪንግ፣ በኮንስትራክሽን፣ በከተማ ግብርና፣ በንግድ እና በአገልግሎት ዘርፍ እንዲሰማሩ የሚያስችል ዝግጅት ተጠናቋል፡፡ ከስደት ተመላሾቹ ወደ አገራቸው ከተመለሱ በኋላ ተደራጅተው መሰማራት የሚፈልጉትን የስራ መስክ ማእከል ያደረገ ስልጠና፣ ብድር፣ የመስሪያ ቦታና ሌሎች ድጋፎች እንዲያገኙ ሁኔታዎች እየተመቻቹ መሆናቸውንም ለማወቅ ተችሏል፡፡

ከስደት ከተመለሱት መካከል አንዳንዶቹ መንግስት ስደተኞቹን ወደ አገራቸው እንዲገቡ ከማድረግ ጀምሮ የማቋቋሚያ ድጋፍ በማድረግ ወደ ልማት እንዲገቡ

ሁኔታዎችን በማመቻቸቱ አመስግነዋል፡፡ መንግሥት በሚያዘጋጀው የሥራ እድል ፈጠራ ላይም ለመሰማራት ፍላጎት እንዳላቸውም ተናግረዋል፡፡

መንግስት ዜጎች በአገር ውስጥ ሰርቶ የመለወጥን ግንዛቤን የማሳደግና ህገ ወጥነትን የመከላከል ስራ ላይ አተኩሮ ሲሰራ ቆይቷል። በተለይ የወጣቶችና የሴቶችን ተጠቃሚነት በማጉላትና የስራ ዕድል ፈጠራን አሁን ካለው በተሻላ በማሳደግ የዜጎችን ህገ ወጥ ስደት ለማቆም የሚደረገውን ጥረት ተጠናክሮ ይቀጥላል።

ከብሄራዊ ኮሚቴው ሪፖርት የተገኘ መረጃ እንደሚያሳየው በ2005 በጀት ዓመት ህገወጥ የሰዎች ዝውውርን ለመከላከል በፌዴራልና በክልልና መገናኛ ብዙኃን እየተከናወነ ያለው የግንዛቤ ማስጨበጥ ጥረት አበረታች መሆኑን ነው። የተለያዩ ኃይማኖት ተቋማት፣የንግዱ ማኅበረሰብ፣ የሠራተኛና ማህበራዊ ተቋማትና ድርጅቶች ህገ ወጥ ስደትን በመከላከል ረገድ አስተዋጽኦ ማበርከታቸውም ሪፖርቱ አመልክቷል።

በአሁኑ ወቅት ጠንካራ አገራዊ ንቅናቄ በመጀመሩ ዜጎች ሕገ ወጥ ስደት ተመራጭ አለመሆኑን በበቂ ሁኔታ እንዲገነዘቡ ማድረግ ተችሏል። በኮሚቴው ሪፖርት መሠረት ህገ ወጥ የሰዎች ዝውውርና ምክንያቶችን በማጥናት፣ ህገ ወጥ ደላሎችን ለፍርድ በማቅረብ ረገድ አንዳንድ ክልሎች የተጠናከረ እርምጃ ቢወስዱም ህገ ወጦችን ተገቢ ፍርድ እንዲያገኙ ያልተንቀሳቀሱ መኖራቸውንም የሚታወቅ ጉዳይ ነው።

መቼም የስደት መልካም የለዉም የሚፈልጉትን እስኪያገኙ ህልም እስኪሳካ ድረስ መውጣት መውረድ መልፋት መውደቅ መነሳት ይበዛል፤ እንደዚያም ሆኖ የማይሳካበት አጋጣሚ ይፈጠራል፡፡ እናም በስደት የተጀመረ ህይወትን ለመለወጥ የማይወጡት ተራራ የማይፈነቀል ድንጋይ የለም ኑሮን ለማሸነፍ የሚደረገው ትግል በጣም አድካሚ፣ አሰልቺ አንዳንዴም ተስፋ አሰቆራጭ ነው።

ይህን የስደት ህይወት አስቀያሚ የሚያደርገው ደግሞ አምነህ ተመክተህበት ይረዳኛል ይደግፈኛል ከዚህ ችግር ያወጣኛል ብለህ ያመንከበት ሰው ሲከዳህ ወይም መፍትሄ ይሰጠኛል ያልከው ሰዉ ሌላ ፈተና ሲሆንብህ አለም ይጨልምብሃል፡፡ ይህ በደል በሁሉም የሰው ልጅ ዘር ላይ የሚደርስ ቢሆንም በሴቶች ላይ ደግሞ ጉዳቱ የከፋ ነው።

ማንም ሴት ከሀገሯ ወደአረብ ሀገር ስትሰደድ ሰርታ ላቧን አፍሳ ከራሷ አልፋ ቤተሰቧን ለመርዳት ለመለወጥ አላማ አድርጋ ነው ስደትን የምትመርጠው። ይህ ደግሞ በአገራችን የስራ አማራጮች ባልነበሩበት ወቅት በሰፊው ይታይ የነበረ ጉዳይ ቢሆንም አማራጮች ከተፈጠሩ በኋላም የቀመበት ሁኔታ አልነበረም።

በአብዛኛዎቹ የአረብ ሀገራት ላይ ከፍተኛ በደል የሚደርስባቸው ሴቶች ለመሆናቸው መረጃዎች ያሳያሉ። በተለይ የአረብ ቤት ውስጥ በሰራተኝነት የሚሰሩ እህቶቻችን በቀን ውስጥ ያለ እንቅልፍ ያለ እረፍት ከ 16 ሰዓታት በላይ መስራት የተለመደ ነው። እረፍት የሚባል ነገር አያውቁም።

ከዚህ ወደ ዓረብ አገር ሲሄዱ የሚያወጡት ገንዘብ በጣም ከፍተኛ እንደሆነ ይታወቃል። ያንን ገንዘብ ይዘው ለመመለስ የማይችሉበት ሁኔታ ግን ይፈጠራል።

ያንን ገንዘብ ማስመለስ ካልቻሉ ደግሞ ለበለጠ ስነ አእምሯዊ ችግር ይዳረጋሉ። መንግስትም ይህንን በመረዳት ነው ጊዚያዊ እገዳ መጣል ያስፈለገው።

አንደ ቤት ባይመቻቸው ወደ ሌላ ቤት ተዘዋውረው መስራት አይችሉም። አንደኛ ፓስፖርታቸው የሚያዘው በአሰሪዎቻቸው እጅ ነው። ሌላው ደግሞ አሰሪዎቻቸው ፓስፖርቱን ለፖሊስ ካስረከቡና እኛ ኮንትራታችንን ሰርዘናል ካሉ ሕጋዊ የነበረች ሴት ሕገወጥ ትሆንና ታፍሳ ወደ ማጎሪያ ቤት እንድትገባ ትደረጋለች።

ከእነዚህ ችግሮች ለማምለጥ ታዲያ ከፍተኛ መስዋእትነት መክፈል የግድ ይሆንባቸዋል። ከሴትነታቸው ጀምሮ የሚጠየቁትን የመፈጸም። ከዚህ በላይ ምን የስብእና ጥሰት አለ? ለዚህም ነው መንግስት ይህንን ሕገ ወጥ ስደትና የዜጎች

መነሳቆል ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መፍትሄ ማግኘት እንዳለበት በማመን የውጭ ጉዞን በጊዜያዊነት መከልከልን የመረጠው።

ይሁንና ይህ ሕብረተሰቡ በተገቢው መልክ ሊረዳው ይገባል። በአረብ አገር የሚኖሩ እህቶቻችን በርካታ ችግሮች እየደረሱባቸው እንደሆነ ለማወቅ የሚያስቸግር አይደለም። ስራ ይሰሩልናል ብለን የምንልካቸው ልጆቻችን ለከፍተኛ ፈተና እየተዳረጉ እንደሚገኙ መረዳት የግድ ይላል።

ሳይወዱ በግድ ወደወሲብ ህይወት እንዲገቡ ይደረጋሉ። በአረብ ሀገር ይህ ስራ ህገወጥ ስለሆነ ወሲብ ፈላጊውዉ ብዙ ነው። በብዙዎች የመታለልና ለበሽታ ተጋላጭ የመሆን እድሉ ከፍተኛ ነው።

ትልቁ ነገር ያለውን ችግር መዘርዘር አይደለም። ይልቁንም ችግሩ እንዴት ይቁም የሚለው ነው። ችግሩ ሊቆም የሚችለው መንግስት የጀመረው ጥረት የህዝብ ድጋፍ አግኝቶ ውጤታማ መሆን እንዲችል ሁሉም ዜጋ የበኩሉን አስተዋጽኦ ሲያደርግ ነው።

ወደ አረብ አገራት የሚሄዱ የሌሎች አገራት ዜጎችም አሉ። ለምሳሌ ያህል ፍልፒኖችን መውሰድ እንችላለን። እነሱ የኢትዮጵያዊያኖች ያህል በደል አይደርስባቸውዉም። ምክንያቱም አንዲት ፍሊፒናዊት ችግር ከደረሰባት ወደ ኤምባሲዋ በመሄድ ቤት የመቀየር መብት አላት። ስለዚህ አንድን ቤት ብትለቅ ሕገወጥ ነሽ በሚል የሚያሳድዳት አካል አይኖርም።

የኢትዮጵያ መንግስትን እንደዚህ አይነቱን አሰራር ለማስፈን ነው የተለያዩ ጥረቶች በማድረግ ላይ የሚገኘው። ይህ ደግሞ እውን የሚሆነው የሕብረተሰቡ ሙሉ ተሳትፎ ሲታከልበት ነው። አገራችን ኢትዮጵያ በግዛቷ የሚገኙ ስደተኞችን በማስተናገድና ሰብዓዊ ክብራቸውን በመጠበቅ ረገድ እያደረገች ያለው ሁለገብ ጥረት ከማንም የተሰወረ አይደለም። ከተለያዩ ጎረቤት አገራት የሚገቡ ስደተኞችን በመቀበል፣ በማስተናገድና በግዛቷ ያሉ በተገቢው ሁኔታ እንዲያዙና ሰብዓዊ ክብራቸው እንዲጠበቅ በማድረግ ረገድ የማትታማ አገር ሆናለች።

አሁን የተቋረጠው ህገወጥ የሰዎች ዝውውር እገዳ ህገወጥ ደላሎች በዜጎች ላይ የሚያደርሱትን በደል ከማስቆምም በተጨማሪ በህግ በኩል ያለውን ክፍተት በበቂ ሁኔታ መሙላት ያስችላል የሚል እምነት መኖሩንም ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተገኙ መረጃዎች ያሳያሉ።

መንግስት  ዜጎቻችን በቤት ሰራተኝነት ወደ ውጭ አገራት ልኮ የማሰራቱ ሥራ በመተው አሰልጥኖ ለተሻለ ስራ መላኩ ለግለሰቦቹም ሆነ ለአገር የሚኖረውን ፋይዳ በመገንዘብ የማስልጠኛ ተቋማትን እያዘጋጀ ይገኛል።  ህገወጥ የሰዎች ዝውውርን ለመቆጣጠር በፌዴራልና በክልል የተጀመሩ ጥረቶች የበለጠ ተጠናክረው እንዲቀጥሉ መንግስት ጥረት እያደረገ ይገኛል።

ይሁን እንጂ ዜጎቿ በሌሎች አገራት እየሄዱ ክብራቸው ሊነካ አይገባም። ለዚህ ዘላቂ መፍትሄ ማምጣት ይጠበቅባታል። መንግስት ይህንን ግምት ውስጥ ያስገባ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ እንዳለም መረጃዎች ያሳያሉ። አንድም አሁን በሳውዲ አረቢያ የተፈጠረውን ችግር በአግባቡ መፍታት በሌላ በኩል ደግሞ ዘላቂ መፍትሄ ማበጀት ናቸው።

ከሳውዲ አረቢያ ተመላኞች ላይ ቅድሚያ ሰጥቶ እየሰራ ያለው የኢትዮጵያ መንግስት እስካሁን ድረስ በዚያች አገር በህገወጥ መንገድ ይኖራሉ ተብሎ ከሚገመተው ቁጥር ከፍተኛውን ያስመለሰ ሲሆን በቀጣይ ጊዜያት ስራውን ለማጠናቀቅ በንቃት እየሰራ ይገኛል።

ይህን ካረጋጋ በኋላ ደግሞ አጠቃላይ ስደትን በሚመለከት ስርዓት ያለው አሰራር ለመዘርጋት የሚያስችል እንቅስቃሴ ያደርጋል። ለዚህ ሁሉ መሳካት የሕብረተሰቡ ተሳትፎ ወሳኝ በመሆኑ ሁሉም ዜጋ የድርሻውን ሊወጣ ይገባል። ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር በመንግስት ጥረት ብቻ ሊገታ አይችልምና ሁሉም የችግሩን አሳሳቢነት ተገንዝቦ ሊሰራ ይገባል።